9ኛ አመት ቁጥር 36

9th Year Nº 36

ባህር ዳር ጥቅምት 30 ቀን 1997 ዓ.ም

Bahir Dar November 9, 2004

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

# ዝክረ-ሕግ

# ZIKRE-HIG

# OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA



| | | | |
|---|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ ብር<br>Price 9.90 | በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE | የ ፖ.ሣ.ቁ<br>312<br>P.o. Box |



## ማውጫ

### ደንብ ቁጥር 16/1996 ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሠራተኞች ያለደመወዝ ልዩ ፈቃድ ስለሚሰጥበት ሁኔታ የወጣ የክልል መስተዳድር ም/ቤት ደንብ

## Contents

### Regulation No.16/2004

A Council of Regional Government Regulation to Provide for conditions of Special leave without pay to civil servants in the Amhara National Regional State.

## ደንብ ቁጥር 16/1996 ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሠራተኞች ያለደመወዝ ልዩ ፈቃድ ለመስጠት የወጣ የክልል መስተዳድር ም/ቤት ደንብ፡፡

## REGULATION NO.16/2004

A COUNCIL OF REGIONAL GOVERNMENT REGULATION ISSUED TO PROVIDE FOR CONDITIONS OF SPECIAL LEAVE WITOUT PAY TO CIVIL SEROVANTS IN THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE.

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 74/1994 ዓ/ም/ እንደተሻሻለ/ በአንቀጽ 41 ሥር ለመንግስት ሠራተኞች ያለ ደመወዝ ልዩ ፈቃድ የሚሰጥበት ሁኔታ ወደ ፊት በሚወጣ ደንብ እንደሚወሰን አስቀድሞ የደነገገ በመሆኑ፣

አንዳንድ የመንግስት ሠራተኞች ደመወዝ የማይከፈልበት ልዩ ፈቃድ እንዲሰጣቸው መ/ቤቶቻቸውንና በአነርሱም በኩል ኮሚሽኑን እየጠየቁ በመሆኑና ይህንንም የሚያስተናግድ ሥርዓት ባለመኖሩ፣

ከዚህ የተነሣ አዋጁን መሠረት በማድረግ ያለደመወዝ ልዩ ፈቃድ መስጮና መከልከያ ሆነው የሚያገለግሉ ግልጽ መመዘኛዎችን አውጥቶ በሥራ ላይ ማዋል በማስፈለጉ፣

የአማራ ብሔራዊ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ተሻሽሎ በወጣው የብሔራዊ ክልሉ ሕገ- መንግስት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 7ና በክልሉ የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 74/1994 ዓ.ም /እንደተሻሻለው/ አንቀጽ 88 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች ሥር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "ያለደመወዝ ለመንግስት ሠራተኞች ልዩ ፈቃድ መስጫ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 16/1996 ዓ/ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ

Whereas, it has been beforehand stipulated under article 41 of the amhara National Regional State Civil Servants Proclamation No.74/2002( as amended ) that the condition of providing civil servants with special leave without pay shall be determined by a regulation to be issued in the future;

Whereas, some civil servants have been asking their respective offices, and through them, the commission, for a provision of a special leave without pay and there does not hitherto exist a system to accommodate such inquiries;

Whereas, as a result of this, it has been found necessary to issue and implement transparent criteria that serve to provide for and prohibit special leave without pay, on the basis of the proclamation;

Now, therefore, the Council of the Amhara National Regional Government, in accordance with the powers vested in it, under the provisions of art. 58, sub art 7 of the revised National Regional Constitution and art. 88, sub art. 1 of the Regional Civil Servants proclamation No. 74/2002 (as amended), hereby issues this regulation as follows:

## PART ONE

## GENERAL

### 1. Short Title

This regulation may be cited as " Civil Servant Special Leave without pay Provision, Council of Regional Government Regulation No.16/2004

### 2. Definitions

Unless the context otherwise requires, in this regulation:

በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

1. "የመንግስት ሠራተኛ" ማለት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 74/1994 ዓ/ም. /እንደተሻሻለው/ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተመለከተው ነው፡፡
2. "ያለደመወዝ ልዩ ፈቃድ" ማለት ደመወዝ ሣይከፈልበት በመንግሥት ሠራተኞች ጥያቄ የሚሰጥ ልዩ የሥራ ጊዜ ፈቃድ ነው፡፡
3." እዋጅ" ማለት የክልሉ መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥረ 74/1994 ዓ.ም /እንደተሻሻለ/ ነው""
4. "ኮሚሽን" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ነው፡፡

1. "Civil Servant" shall take the meaning indicated under art.2, sub art. 1 of the Amhara National Regional State Civil servants' proclamation No. 74/2002 (as amended).
2. "Special Leave Without Pay" means special off duty time leave given without salary up on request by civil servants.
3. "Proclamation" mean the Regional Civil servants Proclamation No. 74/2002 (as mended).
4."Commission" means the Amhara National Regional State Civil Service Commission.

## ክል ሁለት

## አላማና መርሆዎች

## PART TWO

## OBJECTIVE AND PRINCIPLE

### 3. የደንቡ ዓላማ

ደንቡ ሥራና ሠራተኛን ማዕክል ባደረገ አኳኋን ደመወዝ ሳይከፈልበት በመንግስት ሠራተኞች የሚጠየቀው ልዩ ፈቃድ ወጥነትና ፍትሐዊነት ባለው አሠራር በመንግስት መ/ቤቶች በኩል የሚስተናገድበትን ምቹ ሁኔታ የመፍጠር ዓላማ ይኖረዋል፡፡

### 3. Objective of the Regulation

The regulation shall have the objective of creating favorable conditions that a special leave without pay, being sought for by civil servants, be treated and obtain due response by government offices in procedures having uniformity and fairness in a manner central to the promotion of employment-employee relationship

### 4. ያለደመወዝ የሚሰጥ ልዩ ፈቃድ ስለሚመራበት መርህ

ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ በበቂ ምክንያት ደመወዝ የማይከፈልበት ልዩ ፈቃድ እንዲሰጠው ሲያመለክትና ጥያቄውም የመሥሪያ ቤቱን ጥቅም የማይጐዳ ሆኖ ሲገኝ የመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ደመወዝ የማይከፈልበት ልዩ ፈቃድ እንዲሰጠው ሊፈቅድ ይችላል፡፡

### 4. Principle Governing Provision of Special Leave without Pay

Where any civil servant, up on sufficient ground, applies for a special leave without pay, the senior official of the office may authorize the grant for such a leave on condition that the request does not adversely affect the interest of the office;

### 5. አካላዊና ከእምሮአዊ ድካም

### 5. Physical and mental Fatigue

ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ በመንግስት መ/ቤት ውስጥ ከ10 አመታት ላላነሰ ጊዜ ያገለገለ መሆኑን በማረጋገጥ ከሥራው ጋር በተለያየዘ አካላዊና አእምሮአዊ ድካም እንደተሰማው ወይም የስልቹነት ስሜት እንዳደረበት ገልጾ እረፍት እንዲሰጠው ካመለከተ በዚህ ደንብ መሠረት ከ1 ወር ለማይበልጥ ጊዜ ደመወዝ የማይከፈልበት ልዩ ፈቃድ የማግኘት መብት ይኖረዋል፡፡

Where any civil servant applies for a leave ascertaining that he has served for not less than 10 years in government offices and thereby complaining about physical and mental fatigue or feeling of tediousness in relation to his work, he shall be entitled, pursuant to this regulation, to a special leave without pay not exceeding one month.

## 6. በሥራ ወይም በጉብኝት ምክንያት ስለሚሰጥ ፈቃድ

ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ ለሥራም ሆነ ለጉብኝት ጥሪ ደርሶት በአገር ውስጥም ሆነ በባህር ማዶ ለመንቀሳቀስ ሲፈልግ ከ3 ወር የማይበልጥ ደመወዝ የማይከፈልበት ልዩ ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል፡፡ ዝርዝሩ ይህን ደንብ ለማስፈፀም በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

## 6. Leave Grunted due to work or visit

Where any civil servant is called up on either for work or visit at home or abroad and wishes to move thereto, he may be given a special leave without pay, not exceeding 3 months. Details shall be determined by a directive to be issued for the execution of this regulation.

## 7. ዲኘሎማሲያዊ ተልዕኮ

በዲኘሎማሲያዊ ተልዕኮ ወይም ሥራ ላይ እንዲሠማሩ በመንግስት የተመረጡ መሆናቸውን የሚያሣይ ማስረጃ አግባብ ካለው አካል ማቅረብ የሚችሉ ሠራተኞች ባሎች ወይም ሚስቶች የትዳር ጓደኞቻቸው የተጣለባቸውን አደራ በአግባቡ ተወጥተው እስኪመለሱ ድረስ ያለደመወዝ ልዩ ፈቃድ እንዲሰጣቸው ይደረጋል፡፡

## 7. Diplomatic Mission

The husbands or wives of these employees selected by the government to serve in a diplomatic mission or the like activity shall be granted a special leave without pay until such time that there partners return home having properly carried out the duties entrusted up on them provided that the applicants produce an evidence, to that effect, from a competent organ.

## 8. ልዩ ፈቃድን ያለማደመወዝ ስለማራዘም

ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ በአዋጁ አንቀጽ 38፣39 እና 40 ሥር በተደነገገው መሠረት አስቀድሞ ደመወዝ የሚከፈልበት የጋብቻ፣ የሃዘን ወይም ሌላ ማናቸውም ተመሣሣይ ልዩ ፈቃድ ጠይቆ የወሰደ

## 8. Extension of Special Leave Without Pay

Where any civil servant has already taken marital, mourning or any other special leave of similar nature with pay, pursuant to the provisions of articles 38,39 and 40 of the proclamation and where the time taken for the return

እንደሆነና ከቦታው ርቀት የተነሣ የደርሶ መልስ ጉዞው ሊፈጀው የሚገባው ጊዜ ከአቅሙ በላይ በሆነ ምክንያት ከተራዘመ ተጨማሪ ጊዜ ቢኖር ተሰልቶ ለዚሁ ብቻ የሚያገለግልና ደመወዝ የማይከፈልበት ልዩ ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 9. ልዩ ሁኔታ

በሥራው አጋጣሚና ምክንያት የክልሉ መንግስት ንብረት በእጁ ሊገባ የቻለ ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ ለሥራ የተረከባቸውን እቃዎች ወይም መሣሪያዎች ያላስረከበ ወይም የመንግስት ገንዘብ ወይም ንብረት ማባከኑ የተደረሰበት እንደሆነ ከዚህ በላይ የሠፈሩት አንቀጾች ተጠቃሚ አይሆንም፡፡

### 10. ስለቅሬታ አቀራረብ

1. ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ ያለደመወዝ ልዩ ፈቃድ ጠይቆ በመከልከሉ ምክንያት በደል ተፈጽሞብኛል ብሎ ካመነ ቅሬታውን ለኮሚሽኑ የማሰማት መብት አለው፡፡
2. በዚህ ደንብ አፈፃፀም ዙሪያ የሚቀርቡ ጥቆማዎችና ቅሬታዎች በመንግስት ሠራተኞች የቅሬታ አቀራረብና አወሣሰን ሥነ-ሥርዓት ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

### 11. ተጠያቂነት

1. ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ በተጭበረበረ ወይም በሀሰተኛ ማስረጃ ተጠቅሞ ያለ ደመወዝ ልዩ ፈቃድ የወሰደ መሆኑ በመ/ቤቱ ወይም በኮሚሽኑ ኢንስፔክተሮች አማካኝነት የተረጋገጠ እንደሆነ አግባብ ባለው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

journey has, as a consequence, been extended beyond his capacity due to the distance of the place, he may be granted special leave without pay serving the purpose, with any additional time, if so exists, having been calculated thereto.

## PART THREE

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 9. Special Circumstance

Any civil servant who, by virtue of his official duties, the property of the regional state happened to get in to his hands or did not return the properties he had received for work or has been found to embezzle public funds or property, shall not enjoy the benefits of articles stated hereinabove.

### 10. Submission of Grievance

1. Any civil servant who is of the belief that wrong has been committed on him because of his denial of a special leave without pay upon request, shall have the right to submit grievance to the Commission.
2. Allegations and grievances arising from and with regard to the execution of this regulation shall be implemented pursuant to the provisions of the civil servants' grievance presentation and decision making procedural regulation.

### 11. Accountability

1. Where any civil servant is found by his office or the inspectors of the commission to have taken special leave without pay using fraudulent or falsified evidence, he shall be liable in accordance with the relevant provisions of the penal law

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህንን ደንብ በተዛባ መልኩ የሚያስፈፅም ማናቸውም አካል በሕግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 12. የሥልጣን ውክልና

1. ለዚህ ደንበ አፈፃፀም የክልሉ ቢሮዎችና የየወረዳ አስተዳደሮች ከኮሚሽኑ ሙሉ የሥልጣን ውክልና አላቸው፡፡
2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተመለከተው ቢኖርም የክልል ቢሮዎች ለዞን ቅርንጫፎቻቸው የሥልጣን ውክልና ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

## 13. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ይህንን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ኮሚሽኑ ያወጣል፡፡

## 14. ደንቡ ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ መንግስት ዝክረ ሕግ ጋዜጣ ታትመ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ባህር ዳር**
**ጥቅምት 30 ቀን 1997 ዓ.ም**
**ዮሴፍ ረታ**
**የአማራ ብሔራዊ ክልል**
**ርዕሰ መስተዳድር**

2. without prejudice to the provision stipulated under sub-art. 1of this article hereinabove any organ responsible for the execution of this regulation in a distorted manner shall be held liable by law.

## 12. Delegation of Power

1. The Regional bureau and the woreda Administrations shall, for the implementation of this regulation, have complete delegation of power from the commission.
2. Notwithstanding the provision stated under sub-art. 1 of this article hereof, the regional bureau may delegate powers to their respective zonal branches.

## 13. Power to Issue Directives

The commission shall issue directives to execute this regulation.

## 14. Effective Date

This regulation shall come in to force as of the date of its publication in the Ziker-Hig Gazette of the Regional State.

**Done at Bahir Dar**
**This 9th day of November, 2004**
**YOSEF RETA**
**Head of Government of the Amhara National Regional State**